- ኢየሱስ ፈወሰው?

ማርቆስ 1፥41-42

40- ኢየሱስም ለሰውየው በመራራት እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና፣ «እፈቅዳለሁ፣ ንጻ» አለው።

41- እርሱም ወዲያው ከለምጹ ነጻ፤ ከበሽታውም ተፈወሰ።

- ኢየሱስ ለምጻሙን ዳሰሰውና «ንጻ» አለው ሰውየውም ተፈወሰ።

- እግዚአብሔር የሆነው ኢየሱስ ብቻ ነበር ሰውየውን የፈወሰው።

- ኃጢአት ከለምጽ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

- ለምጻሙ ራሱን ከለምጽ ማንጻት እንደማይችል ሁሉ ሰዎች ሁሉ ራሳቸውን ከኃጢአት ማንጻት አይችሉም።

- ሌላ ሰው ሰውየውን ከለምጽ ማንጻት እንደማይችል ሁሉ ማንም ሰው ከኃጢአታችን ሊያድነን አይችልም።

- ኢየሱስ ብቻ ሰውየውን ከለምጽ እንዳነጻው ሁሉ ከኃጢአታችን ሊፈውሰን የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው።

- ኢየሱስ ከኃጢአት ሊያድነን ወደ ዓለም መጣ።
- ኢየሱስ ከሞት ሊያድነን ወደ ዓለም መጣ።

- ኢየሱስ ከሰይጣን ሊያድነን ወደ ዓለም መጣ።

- ሌላ ማንም ሰው ሊያድነን አይችልም፤ ኢየሱስ ብቻ ሊያድነን ይችላል።



## ትምህርት 50

1. ሰይጣን ኢየሱስን ለምን ፈተነው?
ሀ- ምክንያቱም ሰይጣን ኢየሱስ ኃጢአት እንዲሠራ ስለፈለገ።

2. ሰይጣን ኢየሱስ ኃጢአት እንዲሠራ የፈለገው ለምንድን ነው?
ሀ- ምክንያቱም ሰይጣን ኢየሱስ ሰዎችን እንዲያድን ስለማይፈልግ።

3. ኢየሱስ ድንጋዩን ወደ ዳቦ መለወጥ ይችል ነበር?
ሀ- አዎን።
ለ- ኢየሱስ እግዚአብሔር ነበር።
ሐ- ኢየሱስ ሁሉንም ነገር ማድረግ ይችላል።

4. ኢየሱስ ሰይጣንን ከምግብ የበለጠ አስፈላጊው ነገር ምንድን ነው አለው?
ሀ- ኢየሱስ ሰይጣንን የእግዚአብሔርን ቃል ማመን ከምግብ ይልቅ አስፈላጊ መሆኑን ነገረው።

5. ኢየሱስ ቢራብም እንኳ ድንጋዩን ወደ ዳቦ ያልለወጠው ለምን ነበር?
ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ እንዲህ እንዲያደርግ ስላልነገረው።
ለ- ኢየሱስ ሰይጣንን ስለማይታዘዝ።
ሐ- ኢየሱስ እግዚአብሔር አብን ብቻ ስለሚታዘዝ።

6. ሰይጣን በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ ምን እንደተጻፈ ያውቃል?
ሀ- አዎን።

7. ሰይጣን በእግዚአብሔር ቃል ምን አደረገ?
ሀ- ሰይጣን ሰዎችን ለማጥመድ የእግዚአብሔርን ቃል አጣመመ።

8. ሰይጣን ኢየሱስ መላውን ዓለም እንዲቆጣጠር ሥልጣን መስጠት የሚችለው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም አዳም ሰይጣንን በታዘዘው ጊዜ ሰይጣን የአዳም የሰዎች ሁሉና የዓለም ሁሉ ገዥ በመሆኑ ነው።

9. ኢየሱስ ሰይጣንን በምን አሸነፈው?

ሀ- በእግዚአብሔር ቃል።

10. ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል አጣምሟል?

ሀ- አላጣመመም።

ለ- ኢየሱስ በእግዚአብሔር መጽሐፍ እንደተጻፈው የእግዚአብሔርን ቃል ተናገረ።

11. ከኢየሱስና ከሰይጣን የሚበልጠው ማን ነው?

ሀ- ኢየሱስ።

12. ኢየሱስ ከሰይጣን የሚበልጠው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

ለ- ምክንያቱም በመጀመሪያ ሉሲፈርን ፍጹም አድርጎ የፈጠረው ኢየሱስ ስለሆነ ነው።

13. ኢየሱስ በሰይጣንና በአጋንንቱ ላይ ወደ ፊት ምን ያደርግባቸዋል?

ሀ- ኢየሱስ ሰይጣንና አጋንንቱን ሁሉ በዘላለማዊው የእሳት ባሕር ውስጥ ይጥላቸዋል።

- አንድ ቀን ክፉው ንጉሥ ሄሮድስ መጥምቁ ዮሐንስን እስር ቤት አስገባው።

- መጥምቁ ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ ኢየሱስ ምን አደረገ?

ማርቆስ 1፡14



- ኢየሱስ በነበረበት ዘመን ለምጽ መድኃኒት የሌለው በሽታ ነበር።

- እናንተ ለምጽ ቢኖርባችሁ እናንተን የሚያድን ምንም መድኃኒት አልነበረም።

- እናንተ ለምጽ ቢኖርባችሁ ለእናንተ የሚሆን ምንም መፍትሔ አልነበረም።

- እናንተ ለምጽ ቢኖርባችሁ ለእናንተ የሚሆን ምንም እርዳታ አልነበረም።

- ሰውየው ራሱን ከለምጽ ማዳን ችሎ ነበር?

- አልቻለም።

- ምንም የፈውስ መንገድ አልነበረም።

- ሰውየውን ከለምጽ መፈወስ የሚችል ሌላ ሰው ነበር?

- አልነበረም።

- ምንም የፈውስ መንገድ አልነበረም።

- ይህን በሽታ የሚያድን ሐኪም ነበር?

- አልነበረም።

- ምንም የፈውስ መንገድ አልነበረም።

- ሰውየው ወደ ኢየሱስ ለምን መጣ?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ብቻ ሊፈውሰው እንደሚችል ስላወቀ ነው።

- ኢየሱስ ኃጢአት ወደዚህ ዓለም ያስገባውን በሽታ ለመፈወስ ፈለገ።

- ኢየሱስ አጋንንት የያዛቸውን ሰዎች የፈወሰው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ስለ ወደዳቸው ነው።

- ምክንያቱም ኢየሱስ አጋንንት ሰዎችን ባሪያ አድርጐ በማየቱ ያዝን ስለ ነበር ነው።

- በመጀመሪያ ኢየሱስ ዓለምን ሲፈጥር፥ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ነበሩ።

- ነገር ግን አዳምና ሔዋን በእግዚብሔር ላይ ኃጢአትን ከመሥራታቸው የተነሣ ሁሉም ሰዎች የሰይጣንና የአጋንንቱ ባሪያዎች ሆኑ።

- ኢየሱስ ሰዎችን ከሰይጣንና ከአጋንንቱ ባርነት ነጻ ማውጣት ይፈልጋል።

- አንድ ቀን ለምጽ ያለበት ሰው ወደ ኢየሱስ መጣ።

ማርቆስ 1፡40

40- «አንድ ለምፃም ወደ እርሱ ቀርቦ ከፊቱ በመንበርከክ፣ «ብትፈቅድ እኮ ልታነጻኝ ትችላለህ» በማለት ለመነው።

- ለምጽ ምንድን ነው?

- ለምጽ ሥጋን የሚበላ መጥፎ በሽታ ነው።



14- ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ወንጌል እየሰበከ ወደ ገሊላ ሄደ።

- ኢየሱስ አይሁዶችን ማስተማር የጀመረው መቼ ነበር?
- መጥምቁ ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ ነበር።

- ኢየሱስ አይሁዶችን ማስተማር ሲጀምር ዕድሜው ስንት ነበር?
- 30 ዓመት።

- ኢየሱስ አይሁዶችን ስለ እግዚአብሔር ወንጌል አስተማራቸው።

- ኢየሱስ ለሕዝቡ ያስተማረው የእግዚአብሔር ወንጌል ምን ነበር?

- የእግዚአብሔር ወንጌል የሰዎች ኃጢአት ሁሉ በሞት የሚቀጣ ቢሆንም እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን አዳኝ መላኩን የሚያበስር ነበር።

- ሕዝቡን እንዲያድን እግዚአብሔር የሚልከው አዳኝ ማን ነበር?
- ኢየሱስ።
- ኢየሱስ ሌላ ምን አስተማረ?

ማርቆስ 1፡15

15-ኢየሱስ «ጊዜው ደርሶአል፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች፤ ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ!» እያለ ይሰብክ ነበር።

- ኢየሱስ «ጊዜው ደርሶአል የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች» ሲል ምን ማለቱ ነበር?

- ኢየሱስ አዳኙ የሚመጣበትና የእግዚአብሔር መንግሥት የሰይጣንን መንግሥት የሚያሸንፍበት ጊዜ ደርሶአል ማለቱ ነበር።

- ኢየሱስ ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል ማመን እንደሚገባቸው አስተማረ።

- ሰው እግዚአብሔርን ሊያስደስት የሚችልበት ብቸኛ መንገድ ምንድን ነው?
- በእግዚአብሔር ቃል ማመን።

- ኢየሱስ አይሁዶችን ማስተማር ሲጀምር ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ሰዎችን ጠራ።

ማርቆስ 1፡16-20

16- ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲያልፍ፣ ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ ዓሣ አጥማጆች ስለ ነበሩ፣ መረብ ወደ ባሕር ሲጥሉ አያቸው።

17- ኢየሱስም፣ «ተከተሉኝ፤ ሰው አጥማጆች አደርጋችኋለሁ» አላቸው።

18- እነርሱም ወዲያውኑ መረባቸውን ትተው ተከተሉት።

19- ትንሽ እልፍ እንዳለ፣ የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ በጀልባ ሆነው መረባቸውን ሲያበጃጁ አያቸውና፣ ወዲያውኑ ጠራቸው።

20- እነርሱም አባታቸውን ከቅጥር ሠራተኞቹ ጋር በጀልባው ላይ ትተው ተከትለውት ሄዱ።

- ኢየሱስ ሰዎችን ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ የጠራቸው ለምን ነበር?

- ኢየሱስ የጠራቸው ሌሎችን ስለ እግዚአብሔር ማስተማር እንዲችሉ ሊያስተምራቸው ስለ ፈለገ ነበር።



- ሰዎቹ ጋኔኑ ኢየሱስን በመታዘዙ ተገረሙ።

- በኋላ በዚያ ምሽት ምን ተፈጸመ?

ማርቆስ 1፡32-34

32- ጀንበር ከጠለቀች በኋላ፣ ምሽት ላይ የአካባቢው ሰዎች ሕመምተኞችንና በአጋንንት የተያዙትን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ።

33- የከተማዋ ሕዝብ በሙሉ በቤቱ ደጅ ላይ ተሰብስቦ ነበር።

34- እርሱም በተለያየ በሽታ የታመሙትን ብዙዎችን ፈወሰ፤ ብዙ አጋንንትም አወጣ፤ ነገር ግን አጋንንቱ የኢየሱስን ማንነት ያውቁ ስለ ነበር እንዲናገሩ አልፈቀደላቸውም።

- በዚያ ምሽት ሰዎች የታመሙ ሰዎችንና በአጋንንት የተያዙትን ሁሉ ወደ ኢየሱስ አመጧቸው ኢየሱስም ሁሉንም ፈወሳቸው።

- ይህ የሆነው ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።
- ይህ የሆነው ኢየሱስ ሁሉንም ነገር ማድረግ ስለሚችል ነው።

- ኢየሱስ ሁሉንም ሕሙማን ለምን ፈወሰ?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ስለወደዳቸው ነው።
- ምክንያቱም ኢየሱስ ሰዎች ስለታመሙ ያዝን ስለነበር ነው።

- በመጀመሪያ ኢየሱስ ዓለምን በፈጠረበት ጊዜ በሽታ አልነበረም።

- ነገር ግን አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ከሠሩ በኋላ ኃጢአታቸው ወደዚህ ዓለም በሽታን አመጣ።

- ኢየሱስ ለጋኔኑ ምን መለሰለት?

ማርቆስ 1፡25-26

25- ኢየሱስም «ጸጥ በል፤ ከእርሱም ውጣ!» ብሎ ገሠጸው።
26- ርኩሱም መንፈስ ሰውየውን በኀይል ካንፈራገጠው በኋላ እየጮኸ ወጣ።

- ኢየሱስ ጋኔኑ ጸጥ እንዲልና ከሰውየው እንዲወጣ አዘዘው።

- ጋኔኑ ኢየሱስን ታዘዘው?
- አዎን።
- ጋኔኑ ኢየሱስን የታዘዘው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ ነው።
- ምክንያቱም ኢየሱስ ከአጋንንት ይልቅ ኃያል ስለሆነ ነው።

- ሰዎቹ ኢየሱስን ሰውየውን ከጋኔን ነጻ እንዳወጣው ሲመለከቱ ምን አሰቡ?

ማርቆስ 1፡27-28

27- ሕዝቡ በሙሉ በመገረም፣ «ይህ ነገር ምንድን ነው? ሥልጣን ያለው አዲስ ትምህርት መሆኑ ነው! ርኩሳን መናፍስትን እንኳ ያዛል፤ እነርሱም ይታዘዙለታል!» እያሉ እርስ በርስ ተጠያየቁ።
28- ወዲያውም ዝናው በገሊላ ዙሪያ ባሉ ስፍራዎች ሁሉ ተዳረሰ።

- ሰዎቹ ኢየሱስ ሰውየውን ከጋኔን ነጻ ስላወጣው ተገረሙ።



- ኢየሱስ ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ከጠራቸው ሰዎች የአንዳንዶቹ ሥራ ምን ነበር?

- አንዳንዶቹ ዓሣ አጥማጆች ነበሩ።

- አንድ ቀን ኢየሱስ አይሁዶችን ለማስተማር ቅፍርናሆም ወደምትባል ከተማ ሄደ።

ማርቆስ 1፡21

21- ከዚያም ወደ ቅፍርናሆም ሄዱ፤ ኢየሱስም ወዲያው በሰንበት ቀን ወደ ምኵራብ ገብቶ ማስተማር ጀመረ።

- ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም ከተማ በደረሰ ጊዜ ሊያስተምር ወደ ምኩራብ ገባ።

- ምኩራብ ምንድን ነው?

- ምኩራብ አይሁዶች የእግዚአብሔርን መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ የሚገናኙበት ቤት ነው።

- አብዛኛዎቹ አይሁዶች ስለ ኢየሱስ ትምህርት ምን ያስቡ ነበር?

ማርቆስ 1፡22

22- እንደ ጸሓፍት ሳይሆን፣ እንደ ባለ ሥልጣን በማስተማሩ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ።

- አብዛኛዎቹ አይሁዶች በኢየሱስ ትምህርት የተገረሙት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ በኃይልና በብዙ ጥበብ ያስተምራቸው ስለነበር ነው።

- የሕግ መምህራን እነማን ነበሩ?
- ፈሪሳውያን ነበሩ።

- የኢየሱስ ትምህርት ከፈሪሳውያን ትምህርት የሚለየው በምን ነበር?

- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ እግዚአብሔር አብን ያውቀዋል።
- ፈሪሳውያን ግን እግዚአብሔር አብን አያውቁትም።

- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ያውቃል።

- ፈሪሳውያን ግን የእግዚአብሔርን ቃል አያውቁም ።

- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ያምናል።

- ፈሪሳውያን ግን የእግዚአብሔርን ቃል አያምኑም።

- ኢየሱስ በማስተማር ላይ ሳለ በአጋንንት የተያዘ አንድ ሰው ጮኸ።

ማርቆስ 1፥23-24

23- በዚያን ጊዜ በምኩራባቸው ውስጥ የነበረ ርኩስ መንፈስ ያደረበት አንድ ሰው እንዲህ በማለት ጮኸ፤

24- «የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፤ ከእኛ ምን ትሻለህ? ልታጠፋን መጣህን? እኔ ማን እንደ ሆንህ ዐውቃለሁ፤ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ!»

- በመጀመሪያ አጋንንት ከመሆናቸው በፊት አጋንንት ምን ነበሩ?



- በመጀመሪያ አጋንንት ሰይጣንን ተከትለው ክፉ ከመሆናቸው በፊት እግዚአብሔር መልካም አድርጎ የፈጠራቸው መላእክት ነበሩ።

- አጋንንት በእግዚአብሔር በማያምኑ ሰዎች ውስጥ መኖር ይወዳሉ።
- ጋኔን በጮኸው ሰውዬ ውስጥ ይኖር ነበር።

- ጋኔኑ ያስተምር የነበረው ኢየሱስ መሆኑን አውቋል?
- አዎን።

- አጋንንት ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ?
- አዎን።

- አጋንንት ኢየሱስ ፍጹም ቅዱስና ኃጢአትን ሁሉ የሚጠላ መሆኑን ያውቃሉ?

- አዎን።
- አጋንንት፥ ኢየሱስ ከእርሱ ይልቅ ኃያል መሆኑን ያውቃሉ?
- አዎን።

- አጋንንት ኢየሱስን የሚፈሩት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም አጋንንት፥ ኢየሱስ በፈለገው ጊዜ ወደ ዘላለማዊው የእሳት ባሕር ውስጥ እንደሚጥላቸው ስለሚያውቁ ነው።

- ጋኔኑ ኢየሱስ በዚያኑ ጊዜ ወደ ዘላለማዊው የእሳት ባሕር ሊጥለው የሚያስችለው ኃይል እንዳለው ያውቃል።